# ●ዝክረ ቃል ላይ የተጠየቁ ጥያቄዎችና መልሶቻቸው●



አዘጋጅ፡- በትረ ማርያም አበባው ካሣ

(የመጻሕፍተ ብሉያት፣ የመጻሕፍተ ሊቃውንትና የመጻሕፍተ መነኰሳት ትርጓሜ መምህር)

ነሐሴ ፳፣ ፳፻፲፯ ዓ.ም

## ●ዝክረ ቃል ላይ የተጠየቁ ጥያቄዎችና መልሶቻቸው●

**፩. በያዕቆብ እጅ የነበረው የኤሳው ጸጕር ወልደ እግዚአብሔርን ለሞት አሳልፈው የሰጡ የአይሁድ እጅ ምሳሌ ነው ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ ያዕቆብ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው፡፡ ይስሐቅ የገዢው የጲላጦስ ምሳሌ ነው፡፡ እናቱ ርብቃ ለያዕቆብ የኤሳውን የሚመስል ጸጕር በእጆቹ አድርጋለት ነበር፡፡ ይስሐቅ ያንን ዳስሶ በረከትን ለያዕቆብ ሰጥቷል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስም በአይሁድ እጅ ተላልፎ ለጲላጦስ ተሰጥቷል፡፡ ጲላጦስም አንተ የአይሁድ ንጉሥ ነህን ብሎታል፡፡

**፪. ክርስቶስን በአብ ዘንድ ልጅ በመንፈስ ዘንድ መንፈስ ነው ሲል ምን ለማለት ነው? ቀጥሎ በአብ ዘንድ ልጅ በማርያም ዘንድ ሕፃን ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ ክርስቶስ በአብ ዘንድ ልጅ መባሉ የአብ የባሕርይ ልጅ ስለሆነ ነው፡፡ በመንፈስ ዘንድ መንፈስ የተባለው ክርስቶስ በመለኮቱ መንፈስ ስለሆነ ነው፡፡ "በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ" እንዲል (1ኛ ጴጥ.3፥18)፡፡ ይህም ረቂቅነቱን ይገልጻል፡፡ በሐዋርያት ሐዋርያ፣ በነቢያት ነቢይ መባሉ ደግሞ ስለሰውነቱ ነው፡፡ እንደ ሐዋርያት አስተምሯል፣ እንደ ነቢያት ትንቢትን ተናግሯልና (ማቴ.24፥5)፡፡ ሐፀነ-አሳደገ ማለት ነው፡፡ ማደግ ለክርስቶስ የሚነገረው በሥጋው ነው፡፡ ወልድ መባሉ በመለኮቱ ሕፃን መባሉ በሰውነቱ ነው፡፡ ከተዋሕዶ በኋላ ግን መለያየት የለምና ያው አንዱ ወልደ አብ ወልደ ማርያም ይባላል፡፡ ከድንግል ማርያም የተወለደው ሕፃን ወልደ አብ ሆኗልና፡፡

**፫. ማርያም የማትረግፍ አበባ ናት፣ የልብሶቿ መዓዛ ሽቶዎች አሉት፣ በእሾህ መካከል ያበበች የሃይማኖት አበባ ናት ሲል ምን ማለት ነው? ሁለተኛ ሰማይ የተባልሽ ድንግል ሆይ ሲልስ ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ ምንም ያህል ደስ ቢያሰኝን የዚህ ዓለም አበባ ለአጭር ጊዜ ታይቶ የሚጠፋ ነው፡፡ ከዚህ ነበረ ከዚህ ደረሰ የማይባል ነው፡፡ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን አበባ እንላታለን፡፡ ይኸውም ረኀበ ሥጋ ረኀበ ነፍስን የሚያርቅ ፍሬ ሕይወት ኢየሱስ ክርስቶስን ስለወለደችልን ነው፡፡ ድንግል ማርያም ዘለዓለማዊት በመሆኗ የማትረግፍ አበባ ተብላለች፡፡ በእሾህ መካከል ያበበች መባሏ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ ከነበረባቸው ሰዎች መካከል የተገኘች መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለባት በመሆኗ ነው፡፡ የሃይማኖት አበባ የተባለች ሃይማኖታችንን ክርስቶስን ስለወለደችልን ነው፡፡ የልብሶቿ መዓዛ ሽቶዎች አሉት የሚለው አንደኛው በቁሙ ይፈታል፡፡ የጌታ ልብስና የእርሷ ልብስ መዓዛው ደስ የሚያሰኝ ልዩ ነበረና ነው፡፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ በሕፃንነቱ ሳለ ዮሴፍ እንደመጠኑ ወንበር አድርጎ ከፊቱ ያስቀምጠው ነበር፡፡ ብዙዎች የጌታን መልኩን እያዩ ደስ ይላቸው ነበር፡፡ ጌታን ያቀፈው ሰው ልብሱ እስኪያልቅ እስኪበጣጠስ ድረስ ልዩ መዓዛው አይለቅም ነበር፡፡ ጌታን አይቶ ደስ የማይለው የልቡን ኀዘን የማይዘነጋ አልነበረም፡፡ መልኩን ማየት መከራን ያርቅ ነበር" እንዲል (አረጋዊ መንፈሳዊ ድርሳን 24)፡፡ ድንግል ማርያም ሁለተኛ ሰማይ የተባለችበት ምክንያት ከሰማይ ፀሐይ

እንደሚወጣ ከድንግል ማርያምም ፀሐየ ጽድቅ ኢየሱስ ክርስቶስ ተወልዷልና ነው። እንዲሁም ሰማይ ከምድር በላይ እንዳለ እርሷም በቅድስና ከሰው ሁሉ በላይ ናትና ዳግሚት ሰማይ ትባላለች።

፬. ሳይኖረን ሁሉ አለን፣ የሚያውቀን ሳይኖር ብዙዎች ያውቁናል ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ይህ ቃለ ቅዱሳን ነው። ቅዱሳን ሳይኖረን ሁሉ አለን ማለታቸው ስለእግዚአብሔር ብለው ምድራዊ ገንዘባቸውን ቢያጡም ሁሉ የእርሱ የሆነ እግዚአብሔርን በጸጋ ስለሚዋሐዱት ሳይኖረን ሁሉ አለን ይላሉ። የሚያውቀን ሳይኖር ብዙዎች ያውቁናል የሚለው ደግሞ ቅዱሳን እዩኝ እዩኝ የማይሉ በዚህ ዓለም ሲኖሩ ራሳቸውን ሠውረው የሚኖሩ ስለሆኑ ብዙ ሰው አያውቃቸውም። የሚያውቀን ሳይኖር ማለታቸው ስለዚህ ነው። ብዙዎች ያውቁናል ማለታቸው ቅዱሳን መላእክት ከሰው ልጆች እጅግ በጣም ስለሚበዙና ጻድቃንን ደግሞ ስለሚያውቋቸውና በብዙ መልኩ ስለሚረዷቸው ነው።

፭. ማርያም የመመኪያችን ዘውድ፣ የዳዊት መሰንቆ የሰሎሞን ዘውድ ናት ሲል ምን ማለት ነው? ድንግል ማርያም በቤተ መቅደስ የተተከለች ሎሚ እንዲሁም የጴጥሮስ ቁልፍ ናት ሲልስ ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ድንግል ማርያም የመመኪያችን ዘውድ የተባለችበት ምክንያት ብዙዎች ለምሳሌ ታላቁ ኢዮስያስ፣ ንጉሥ ዳዊት፣ ንጉሥ ሰሎሞንና ሌሎችም ነገሥታት ነግሠው ዘውድ ቢደፉም ሰውን ከመርገመ ሥጋ ከመርገመ ነፍስ ማዳን ግን አልተቻላቸውም ነበር። እንኳን ከመርገም ሊያድኑን እነርሱም በመርገም ተይዘው ይኖሩ ነበር። ድንግል ማርያም ግን መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ ሳይኖርባት በንጽሕናዋ ከሰው ልጆች ሁሉ በልጣ ብትገኝ መርገምን የሚያጠፋ ንጉሠ ነገሥት ክርስቶስን ወልዳልናለችና የመመኪያችን ዘውድ እንላታለን። ዳዊት መሰንቆ እየመታ እግዚአብሔርን ያመሰግን ነበር። "...ይነሥእ ዳዊት መሰንቆሁ ወይዜምር..." እንዲል (1ኛ ሳሙ.16፥23)። መሰንቆ የእመቤታችን ምሳሌ ነው። ሳኦል የመሰንቆውን ድምፅ ሰምቶ ይድን እንደነበረና የመሰንቆ ድምፅ ሰውን ደስ እንደሚያሰኝ ፈውሰ ሥጋን ፈውሰ ነፍስን የሚሰጥ ደስ ይበላችሁ ብሎ ከኀዘን ያጽናናን ክርስቶስም ከድንግል ማርያም ተወልዷልና የመሰንቆው ድምፅ የጌታ ምሳሌ ነው። የሰሎሞን ዘውድ መባሏ ሰሎሞን በዘውዱ ምክንያት ከብሮ እንደሚኖር እኛም በእርሷ ምክንያት ጌታ ተወልዶልን በጌታ ከብረናልና ነው። አንድም ንጉሥ በዘውድ ይታወቃል። ዘውድ የድንግል ማርያም ምሳሌ ከእርሷ የተወለደው ጌታ የሰሎሞን ምሳሌ ነው። ሰሎሞን ማለት ሰላማዊ ማለት ነው። በባሕርዩ ሰላም የሆነ ሰላማዊ ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ ነውና። በቤተ መቅደስ የተተከለች ሎሚ የተባለችው በደብተራ ኦሪት ከሌሎች በትር ተለይታ ለምልማ ስለተገኘችው የአሮን በትር የተነገረ ነው። መቅደስ ያለው በደብተራ ኦሪት ስለተተካ ነው። "ወኮነ በሳኒታ ወቦአ ሙሴ ወአሮን ውስተ ደብተራ ዘመርጡል ወናሁ ሠረጸት በትሩ ለአሮን እንተ ቤተ ሌዊ ወአውፅአት ቈጽለ ወጸገየት ጽጌ ወፈረየት ከርካዕ" እንዲል (ዘኁ.17፥8)። ይህቺ በትር

ውሃ ሳያጠጧት ለምልማ እንደተገኘች ሁሉ ድንግል ማርያምም ያለ ወንድ ዘር በድንግልና ጌታን ፀንሰዋለችና ነው። ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጴጥሮስን የመንግሥተ ሰማያት መክፈቻዎችን እሰጥሀለሁ ብሎት ነበር። አሁን በሰማይ ቁልፍ ኖሮ አይደለም። በቁልፍ ቤትን ከፍተን እንደምንገባ ለመንግሥተ ሰማያት ማስገቢያ ምክንያት የሚሆን ሀብተ ክህነትን እሰጥሀለሁ ሲለው ነው (ማቴ.16፥19)። ድንግል ማርያም የጴጥሮስ ቁልፍ የተባለችው በምልጃዋ ወደ መንግሥተ ሰማያት መርታ የምታስገባ በመሆኗ ነው።

፳. የቃል ማደሪያ፣ የጨረቃ ክበቡ፣ የፀሐይ ሙቀቱ የሆንሽ ድንግል ሆይ ደስ ይበልሽ ሲል ምን ማለት ነወ? የአንቺን ፍሬ የበሉ ብልኻተኛ ይሆናሉ። የምድር ነገሥታት የእግርሽን ትቢያ ይልሳሉ ሲል ምንድን ነው? ድንግል ማርያምን ለሙሴ እኅቱ ብሎ ለዳዊት ልጁ ሲላት ምን ማለት ነው?

መልስ፦ የቃል ማደሪያ የሚለው ቃለ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን በማሕፀኗ ስለኖረ ነው። የጨረቃ ክበቡ የተባለች ከጨረቃ ክበብ ብርሃን ይወጣል። ከድንግል ማርያምም የዓለም ብርሃን ኢየሱስ ክርስቶስ ተወልዷልና ነው (ዮሐ.8፥12)። የፀሐይ ሙቀቱ ማለቱ ከፀሐይ ሙቀት እንደሚገኝ ሁሉ ምንም እንኳ በሥጋ እናቱ ብትሆን እርሷን የፈጠራትም እርሱ ራሱ በመሆኑ ነው። "ድንግል ወለደቶ ለገባሪሃ። ድንግል ፈጣሪዋን ወለደችው። ወለሊሁ ፈጠረ ወላዲቶ። እርሱ ራሱም እናቱ ፈጠረ" እንዲል (ሃይ.አበ.47፥2)። የአንቺን ፍሬ የበሉ ብልኻተኛ ይሆናሉ ያለው የአንቺ ፍሬ ብሎ የገለጸው ክርስቶስን ነው። የክርስቶስን ሥጋና ደም የሚበሉ ጠቢባን ይሆናሉ ማለት ነው። የምድር ነገሥታት የእግርሽን ትቢያ ይልሳሉ የሚለው በታላቅ ሰው ፊት ከእግሩ አጠገብ መውደቅ የትሕትና ምልክት ነው። ወድቀው ሲነሡ ከግንባራቸው አቧራ ይኖራልና ይህንን ለመግለጽ ይልሳሉ አለ። ምሥጢሩ ግን የምድር ነገሥታት ለታላቂቱ ለአንቺ በትሕትና ይገዛሉ ማለት ነው። ድንግል ማርምን የሙሴ እኅቱ ያላት በየዋህነቷ ነው። "ወሙሴሰ ብእሲ የዋህ ውእቱ ጥቀ እምነ ኵሉ ዕጓለ እመሕያው ዘሀለወ ውስተ ምድር" እንዲል (ዘኊ.12፥3)። ድንግል ማርያምም የዋሂት ርግብ በመሆኗ የሙሴ እኅት ተብላለች። የዳዊት ልጅ ያለበት ምክንያት ዳዊት ትንቢት ሲናገር ልጄ ብሎ ተናግሮላታልና ነው። "ስምዒ ወለትየ ወርእዪ ወአፅምዒ እዝነኪ፤ ወርስዒ ሕዝበኪ ወቤተ አቡኪ" እንዲል (መዝ.44፥10)።

፳. መስቀል ያረጀውን ዓለም አሳመረ ሲል ምን  ማለት ነው?

መልስ፦ በማድረጊያው አድራጊውን ለመግለጽ ነው። ዓለም በኃጢአት ጎስቍሎ፣ ክፋት ሥር ሰዶ፣ ሰው ሁሉ በጨለማ ተውጦ ይኖር ነበር። ይህንን ታሪክ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ተሰቅሎ ቀይሮታል። ያረጀውን ዓለም በደሙ አጥቦ አድሶታል አሳምሮታልና ይህንን ለመግለጽ ነው። ይህ የተደረገው በመስቀል ነውና።

፳. እስመ ሚካኤል እግዚእነ [ሚካኤል ጌታችን ነውኮ] ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፡- መላእክት ከእግዚአብሔር እየተላኩ ሰውን ይረዳሉ:: በጸጋ ሰውን መርዳታቸውን ለመግለጽ በጸጋ ቅዱሳን እንደሚባሉ ጌታም ይባላሉና:: መስፍኑ ጌዴዎን መልአኩን "ጌታዬ" እንዳለው ያለ ነው:: "...ወአስተርአዮ መልአከ እግዚአብሔር ወይቤሎ እግዚአብሔር ምስሌከ ጽኑዐ ኀይል:: ወይቤሎ ጌድዮን ኦሆ እግዚኦ እግዚእየ..." እንዲል (መሳ.6፥12-13):: በዚህ አግባብ በጸጋ ጌታችን ነው ተብሏል:: በባሕርዩ ጌታ የሆነ ግን እግዚአብሔር ብቻ ነው::

፱. ዓውደ ዓመት ለባርኮ እምጽርሐ አርያም ጌልጌል ንዒ ማለቱ ምን ማለት ነው? ፍጡር ሆኖ ከዓለመ ፈጣሪ መውጣት ይቻላል? ጌልጌል ማለትስ ምን ማለት ነው?

መልስ፡- ጌልጌል የሰማይ ሌላ ስሙ ነው:: ሰማይ ኤርሞን፣ ፈለክ፣ ጌልጌል፣ አርያም...ወዘተ የመሳሰሉ ስሞች አሉትና:: እና ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ስሞች ተከታትለው ሲመጡ አንዱ ቅጽል ስለሚሆን ነው ጌልጌል የተባለ ሰማይ ብዬ የተረጎምኩት:: ከአርያም ነይ ማለቱ ጻድቃን አሁን ካሉበት ዓለም ወደዚህ ዓለም መምጣት የሚችሉበት ሁኔታ ስላለ ነው:: ለዚህ ማስረጃው የሙሴና የኤልያስ በደብረ ታቦር መምጣት ነው (ማቴ.17፥3):: ድንግል ማርያምም በተሰጣት ጸጋ ትባርከን ዘንድ ዓውደ ዓመት ለባርኮ ንዒ እንላታለን::

፲. ኢኀደጋ ለምድር እምቅድመ ዓለም ዘእንበለ ካህናት ወዲያቆናት ካለው እምቅድመ ዓለም ያለው ምን ዓለም ነው? ካህናት ዲያቆናት ያላቸውስ እነማን ናቸው?

መልስ፡- ከዚህ ዓለም ያለው ሰውን ነው:: "እስመ አፍቀሮ እግዚአብሔር ለዓለም" ሲል ሰውን ወዷልና ተብሎ ይተረጎማልና (ዮሐ.3፥16):: ካህናት ዲያቆናት የሚላቸው ቅዱሳን መላእክት ናቸው:: እግዚአብሔርን በምስጋና የሚያገለግሉ በመሆናቸው ካህናት ይባላሉ:: ሰው ከመፈጠሩ በፊትም ምድርን ያለ ካህናት አልተዋትም መባሉ መላእክት ስለነበሩ ነው:: ሰው ዓርብ ሲፈጠር ከዚያ በፊት እሑድ ተፈጥረው እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ቆይተዋልና::

፲፩. ታቦት ዘዶር ዘሲና ማን ናት? በሰማይ ታቦት አለ?

መልስ፡- ታቦት ዘዶር ዘሲና ያላት እግዚአብሔር ለሙሴ በደብረ ሲና የሰጠው ታቦት ናት:: ዘሲና (የሲና) የሚለው ይህንን ይገልጽልናል:: ዘዶር የተባለችበት ምክንያት ዱር ዱሩን ይዘዋት በመሄዳቸው ነው:: በሰማይ ታቦት የለም:: በሰማይ ያለችው ታቦት እየተባለች የምትነገር ራሷ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናት:: "ወምስሌሆሙ ታቦት ዘዶር እንተ ይእቲ እግዝእትነ ማርያም" እንዲል (ቅዳሴ ማርያም)::

፲፪. እንበለ ትሣረር ምድረ ገነት ሀለወት ስብሕት ያለው እንዴት ነው?

መልስ፡- የፍጥረታት መታሰባቸው ከመፈጠራቸው ይቀድማል:: እንበለ ትሣረር ምድረ ገነት (የገነት ምድር ሳትፈጠር) በፊት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የተመሰገነች ሆና ነበረች ይላል:: በልበ ሥላሴ ታስባ ትኖር ስለነበረ ነበረች አለ እንጂ

በአካል ያን ጊዜ ኖራ አይደለም:: በልበ ሥላሴ በመታሰብ ፍጥረታት ሁሉ እኩል ናቸው:: በሥላሴ ዘንድ ቀድሞ ያልነበረ ሐሳብ በኋላ አይታሰብምና:: ድንግል ማርያም ተለይታ መጠራቷ ከፍጥረታት ሁሉ ንጽሕት ሆና ብትገኝ የክብሯን ብልጫ ለመግለጽ ነው::

**፲፫. ቅዱስ ያሬድ የኪሩቤል የክንፎቻቸው ድምፅ አይሰማም ይላል:: ሕዝ.10፥5 ላይ ደግሞ ወይሰማዕ ድምፀ ክነፊሆሙ ይላል:: አይጋጭም?**

መልስ፦ አይጋጭም:: ነቢዩ ሕዝቅኤል ይሰማል ማለቱ መስማቱ በራእይ ስለሆነ ነው:: አካላቸውንም አየሁት ብሎ ተናግሯልና:: ቅዱስ ያሬድ የክንፎቻቸው ድምፅ አይሰማም ማለቱ በሥጋዊ ጆሮ ከመሰማት የራቀ በመሆኑ ነው:: መላእክት በተፈጥሯቸው በሥጋዊ ዓይን አይታዩም በሥጋዊ ጆሮ አይሰሙምና:: ሕዝቅኤልም ማየቱና መስማቱ በራእይ እንጂ በሥጋዊ ጆሮና በሥጋዊ ዓይን አይደለምና::

**፲፬. እሳት መንበሩ ማይ ጠፈሩ ለደቅስዮስ ለእግዚአ ኵሉ ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ ለእግዚአብሔር በባሕርዩ የሚነገሩ ነገሮች ለቅዱሳን በጸጋ ይነገራሉ:: እግዚአብሔር እግዚአ ኵሉ ሲባል ፍጹም ሁሉ ነው:: ለምሳሌ ኢየሱስ ክርስቶስ "የዓለም ብርሃን" ሲባል በባሕርዩ ብርሃን መሆኑን ለመግለጽ ነው (ዮሐ.8፥12):: ሐዋርያት የዓለም ብርሃን ሲባሉ ግን በጸጋ ሲሆን አንጻራዊም ነው (ማቴ.5፥14):: መንበር፣ ጠፈር የሚሉት ቃላት ለእግዚአብሔር ሲነገሩ ባሕርይን ያመለክታሉ:: እሳት መንበሩ ማለት የእግዚአብሔር ባሕርዩ ኀያል ነው ማለት ነው:: ማይ ጠፈሩ ማለት እግዚአብሔር በባሕርዩ ኃጢአትን ይቅር የሚል መንጽሒ ነው ማለት ነው:: ደቅስዮስ እግዚአ ኵሉ መባሉ ግን የጸጋ ጌትነት እንዳለው ለመግለጽ ነው:: እሳት መንበሩ ማይ ጠፈሩ ማለቱ ደቅስዮስ በጸጋ ኀያል፣ ይቅር ባይ መሆኑን ያመለክታል::

**፲፭. እምደቂቀ ሌዊ አርአየ ሰብዓተ ሥርዓታተ ይላል:: ምን ማለት ነው? እነማንስ ናቸው?**

መልስ፦ በብሉይ ኪዳን ካህናት የሚሆኑት ከነገደ ሌዊ የሚወለዱት ነበሩ:: ሆኖም ግን የክህነት አገልግሎታቸው በሰባት የተከፋፈለ ነበር (ዘኁ.3፥23-38):: አገልግሎታቸውም ሙሴ አሮንን ሾሟል:: አሮን ሊቀ ካህናት እንደመሆኑ በዓመት አንድ ጊዜ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ገብቶ ለሕዝቡ ይለምናል:: አልዓዛርና ይታምር መሥዋዕተ ሠርክና መሥዋዕተ ነግህን ይሠዋሉ:: ናዳብና አብዩድ መሥዋዕቱን አርደው አወራርደው ያቀርባሉ:: ደቂቀ ጌድሶን የደብተራ ኦሪትን መጋረጃ ይሸከማሉ:: ደቂቀ ቀዓት ታቦቱን፣ ማዕዱን፣ መሠዊያውን፣ መቅረዙን ይሸከማሉ:: ደቂቀ ሜራሪ የደብተራ ኦሪት ምሰሶዎችን፣ ቀልፎቿን፣ ካስማዎችንና መምቻቸውን ይሸከማሉ (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 9 ትርጓሜ):: በደቂቀ ሌዊ አምሳል የአሁኗ ቤተክርስቲያንም ሰባት የክህነት አገልግሎቶች አሏት:: ፖትርያርክ፣ ጳጳሳት፣ ኤጲስ ቆጶሳት፣ ቀሳውስት፣ ዲያቆናት፣ ንፍ*ቀ ዲያቆናትና ከዚያ በታች ያሉት እንደ አንድ ተቆጥረው ሰባት ይባላሉ:: አንዱ የአንዱን አገልግሎት ተላልፎ አይሠራም::

፲፮. ኪሩቤል መንበሩን ከተሸከሙ ወዴት ነው የሚሄዱ ኀበ አንጻረ ቀዳማዊ የሐውሩ ይላልና፡፡ እውነትስ ከመንበሩ በታች በአካል አሉ? ቀዳማዊ ያለውስ በኪሩቤል ዘንድ ምን ቀዳማዊ አላቸው? ሁላቸው በሁሉ አሉ አይደለምን፡፡ ለምሳሌ ገጸ ሰብእ ነው ከተባለ ምኑ ገጸ ሰብእ? አራት በአራት 16 ስለሆኑ በገጸ አንበሳ ያለው ገጸ ሰብእ ነው? ወይስ በሌሎቹ በሦስቱ? አንዱ ከወገቡ በላይ አራት ከሆነ ምንም እንኳ ሐሳቡ መልካም (በጎ) ቢሆን በአራትነቱ ነው የሚያስብ ወይስ በአንድነቱ?

> መልስ፦ እግዚአብሔር በመደበኛነት የሚገለጥበት ሰማይ መንበረ ጸባዖት ነው፡፡ ኪሩቤልም በመደበኛነት የሚሸከሙት ከሰማይ ውዱድ ሆነው ነው፡፡ እግዚአብሔር በመንበረ ጸባዖት የተወሰነ ሆኖ አይደለም፡፡ በሁሉ ቦታ ያለና የሚኖር ነውና፡፡ ያ በመንበረ ጸባዖት በዘፈቀደ የሚገለጠው እግዚአብሔር ከጠፈር በታች በምድርም ለተለያዩ ቅዱሳን በልዩ ልዩ አምሳል ተገልጧል ይገለጣልም፡፡ ለምሳሌ ለአብርሃም በሰው አምሳል መገለጡ ይጠቀሳል፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር ለቅዱሳን ሰዎች ወደሚገለጥበት ቦታ ሁሉ ኪሩቤልም ታዛዦች ናቸውና ይሔዳሉ፡፡ ይህ አካሄዳቸውን ለመግለጽ የሐውሩ ተብሏል፡፡ አዎ ከረቂቅ መንበሩ በታችም በረቂቅ አካላቸው አሉ፡፡ ኪሩቤል ከወገብ በላይ 16 ከወገብ በታች 4 ናቸው (ሕዝ.10፥14፤ ራእ.4፥6)፡፡ ከወገብ በላይ እያንዳንዱ ገጸ ሰብእ፣ ገጸ ንስር፣ ገጸ ሰብእ፣ ገጸ አንበሳ አለው፡፡ ዮሐንስ ወንጌላዊ ፊት ለፊት ባየበት ተናግሯል እንጂ እያንዳንዱ አራቱንም ገጾች አሏቸው፡፡ ፊት ለፊት ባለው ገጽ አንዱ ስለሆነ ያለው እርሱ ባመለከተበት ይከተሉታልና፡፡ ገጸ ንስርና ገጸ ሰብእ አንጻር ናቸው፡፡ ገጸ አንበሳና ገጸ እንስሳ አንጻር ናቸው፡፡ ከወገብ በታች አንድ ከወገብ በላይ አራት የሆነው አንዱ ኪሩብ ሐሳቡ አንድ ነው፡፡ እንኳ የአንዱ የአራቱ ኪሩቤል [16ቱ ገጾት] ሐሳባቸው አንድ ነው፡፡ ለእኛ ለሰዎች ሁለት ጆሮ ቢኖረንም አንድነታችንንና አንድ ሐሳብ ማሰባችንን እንደማይቀይረው ሁሉ ኪሩቤልም ከወገብ በላይ አራት መሆናቸው የሐሳብ ልዩነትን አይፈጥርባቸውም፡፡

፲፯. ብፁዓን ካህናት ጽርሐ አርያም ያድራሉ ያጥናሉ ይላል፡፡ ተክለ ሃይማኖትስ ሄዶ አጠነ ይባላል፡፡ በአካል ነው ወይስ በራእይ?

> መልስ፦ ከዚህ ብፁዓን ካህናት ያላቸው 24ቱን ካህናተ ሰማይ ነው (ራእ.5፥6)፡፡ ያድራሉ ማለቱ በዚያ መኖራቸውን ለመግለጽ ነው፡፡ ያጥናሉ ማለቱ ጸሎትን ወደ እግዚአብሔር ያሳርጋሉ ማለት ነው፡፡ ተክለ ሃይማኖት ከ24ቱ ካህናተ ሰማይ ጋር 25ኛ ሆኖ አጠነ እየተባለ መነገሩ በአካለ ነፍስ ነው፡፡ በረቂቁ ዓለም ከረቂቃኑ መላእክት ጋር በረቂቅ አካለ ነፍሱ በረቂቅ ማዕጠንት ለእግዚአብሔር መሥዋዕተ ጸሎትን አቀረበ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ በአካለ ነፍስ ሄዶ ነው እንጂ በራእይ አይደለም፡፡

፲፰. ሰማዕታት ወደ ሰማዕትነት ሲገቡ ሦስት ስሞችን ይይዛሉ ሲል ምን ማለት ነው?

> መልስ፦ ሦስት ስሞች የተባሉ አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ናቸው፡፡ ሰማዕታት እነዚህን ይዘው ሰማዕትነትን ይፈጽማሉ ማለት በሥላሴ አምነው ስማቸውን ጠርተው ምስክር ይሆናሉ ማለት ነው፡፡

፲፱. ለአንተ የመንግሥተ ሰማያት መክፈቻ የተሰጠህ የሃይማኖት ዐለት ጊዮርጊስ ሆይ ወደ ክርስቶስ የሠርግ ቤት እንገባ ዘንድ ክፈትልን ሲል ምን ማለት ነው? የሠርግ ቤት ሲል እንዴት ነው?

መልስ፦ የሠርግ ቤት ዘመዶች ከሙሽራው ጋር ደስ የሚሰኙበት የደስታ ቤት ነው። የክርስቶስ የሠርግ ቤት የተባለች መንግሥተ ሰማያት ናት። በዚያች የክርስቶስ ዘመዶች የተባልን ክርስቲያኖች ክርስቶስ ነግሦልን ደስ ብሎን እንኖራለንና መንግሥተ ሰማያትን የሠርግ ቤት አላት። ጊዮርጊስን ክፈትልን ማለታችን በምልጃህ ርዳን ለማለት ነው።

፳. ይህቺ መቅደስ የሰማዕታትና የቅዱሳን ሁሉ እናታቸው ናት ሲል እንዴት ነው?

መልስ፦ ይህ ስለቤተክርስቲያን የተነገረ ነው። ቤተክርስቲያን የቅዱሳን ሁሉ እናታቸው ናት መባሏ ቅዱሳን ሁሉ ተጠምቀው ልጅነትን ያገኙባት በመሆኗ ነው።

፳፩. አፍላገ ወንጌሉ የተባሉ እነማን ናቸው?

መልስ፦ አፍላገ ወንጌሉ የተባሉ ሐዋርያት ናቸው። በወንዝ ውሃ ይሄድበታል። ሐዋርያትም የሕይወት ውሃ ክርስቶስ ያስተማረውን ትምህርት ያስተምራሉና አፍላገ ወንጌሉ ተብለዋል።

፳፪. በወንጌል የተጻፈች በራሷ ላይ የመስቀል ምልክት ያለበት አክሊል ያላት የድንግል ክብሯና ትልቅነቷ ፍጹም ድንቅ ነው ሲል እንዴት ነው?

መልስ፦ ይህ ስለእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የተነገረ ነው። በወንጌል የተጻፈች መባሏ ስለድንግል ማርያም ወንጌላውያን ጽፈዋልና ነው። የመስቀል ምልክት ያለባት መባሏ መከራ መቀበሏን ያመለክታል። መስቀል መከራ ተብሎም ይተረጎማልና። በሌላ መልኩ ድንግል ማርያም ለቅዱሳን ስትገለጽ የመስቀል ምልክት ያለበት አክሊል አድርጋ በንግሥት አምሳል ትገለጻለችና በመገለጫዋ ለመግለጽ ነው።

፳፫. ጻድቃንን ማርና ወተትን የምታፈስ አዲስ ምድርን ያወርሳቸዋል ሲል ምን ማለት ነው? ማርና ወተት በሰማይ አለ ወይ?

መልስ፦ በሰማይ ማርና ወተት የለም። ማር የሚወደድ ጣፋጭ ምግብ እንደሆነ ሁሉ ወተትም ተወዳጅ መጠጥ ነው። አንድ ሀገር ማርና ወተትን ያፈሳል ከተባለ ምቹ ቦታ ነው ማለት ነው (ዘፀ.3፥8)። መንግሥተ ሰማያትን ማርና ወተትን የምታፈስ አዲስ ምድር ያላትም የማያልቅ ተድላ ደስታ የሚደረግባት ለማለት ነው።

፳፬. እግዚአብሔር የበቀል ሰይፍ በእጁ አለ ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ እግዚአብሔር በቀለኛ እንደሆነ በመጽሐፍ ቅዱስም ተጽፏል። "እግዚአብሔር የበቀል አምላክ ነው። የበቀል አምላክ ተገለጠ" እንዲል (መዝ.93፥1)። በቀለኛ ነው

ማለትም በሰው በጥፋቱ ልክ ይፈርድበታል ማለት ነው። ፊታሒነቱን ይገልጻል። በቀለኛ ነው ማለት ፈራጅ ነው ማለት ነው።

**፳፰. ስለዚህም የቅዱስ ወንጌል መምህራን እንደፈጣሪ ለድንግል ማርያምና ለመስቀል እንድንሰግድ አዘዙን ሲል ምን ማለት ነው? አምኖ የማርያምን ስም የጠራ ሁሉ ይድናል ሕይወትንም ያገኛል ሲልስ እንዴት ነው?**

መልስ፦ እንደፈጣሪ ለማርያምና ለመስቀል እንስገድ ማለት ለፈጣሪ የባሕርይ ስግደት እንደምንሰግድ ሁሉ ለማርያምና ለመስቀል ደግሞ የጸጋ ስግደትን እንስገድ ማለት ነው። እንጂ ለማርያምና ለመስቀል የምንሰግደው ስግደት ለፈጣሪ እንደምንሰግደው የባሕርይ ስግደት ነው ማለት አይደለም። "ቅዱስ አባት ሆይ እነዚህን የሰጠኸኝን እንደ እኛ አንድ እንዲሆኑ በስምህ ጠብቃቸው" እንደሚለው ነው (ዮሐ.17፥11)። ክርስቶስ አብን እንደእኛ ሲል የአብና የእርሱ አንድነት የባሕርይ አንድነት መሆኑ የታወቀ ነው። እንደእኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ ብሎ ለሐዋርያት ሲናገር ደግሞ እኛ በባሕርይ አንድ እንደሆንን ሐዋርያት በጸጋ አንድ ይሆኑ ዘንድ ማለት ነውና። አምኖ የማርያምን ስም የጠራ ይድናል ማለት በእግዚአብሔር አምኖ በድንግል ማርያም አማላጅነት ተማምኖ አድኝኝ ቢል ይድናል ማለት ነው። ከእግዚአብሔር በተሰጣት ጸጋ ሰውን ታድናለችና።

**፳፱. ድንግል ማርያምን አደባባዮቿ የእውነት ሜዳዋ የዕንቍ፣ የማዳን ደጅ፣ አዲስ ግንብ ናት ሲል ምን ማለት ነው? እመቤቴ ሆይ አደባባይሽ የመረግድ ቅጽሮችሽ የከርከዴን ናቸው ሲልስ ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ አደባባዮቿ፣ ሜዳዋ እያለ የገለጸው ሰውነቷን ነው። ድንግል ማርያም አደባባዮቿ የእውነት ናቸው ማለት እውነተኛ ናት ማለት ነው። ሜዳዋ የዕንቍ የሚለው ዕንቍ ጽሩይ እንደሆነ ሁሉ ሰውነቷ ርስሐት የሌለበት ጽሩይ መሆኗን ይገልጻል። የማዳን ደጅ ሲል ማዳን ያለው ልጇን ክርስቶስን ነው። እርሷ ደጅ መባሏ በደጅ ይገቡበታል ይወጡበታል። ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስም ከእርሷ ተፀንሶ ከእርሷ ተወልዷልና ነው። አደባባዮቿ የመረግድ፣ ቅጽሮቿ የከርከዴን የሚለውም ሰውነቱ ከበደል የነጻ ንጽሕተ ንጹሓን ቅድስተ ቅዱሳን መሆኗን ያመለክታል። አዲስ ግንብ ያላት ንጉሥ ክርስቶስ የኖረባት ለማለት ነው። አዲስ ማለቱ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለባት ንጽሕት በመሆኗ ነው።

**፳፲. ጴጥሮስ ጳውሎስን ወንድሜ ጳውሎስ ሆይ ጨክን አትጠራጠርም ከዚህ በኋላ አንሞትም አለው ሲል እንዴት ነው? ጳውሎስ ተጠራጥሮ ነበር?**

መልስ፦ ይህ ጳውሎስ መጠራጠሩን አይገልጽም። በመከራ ያለ ሰው መከራው ሲበዛበት ይጨነቃል፣ ተስፋ ያለው ሁሉ አይመስለውም። ስለዚህ በዚህ ጊዜ አይዞህ ጨክን፣ አትጠራጠር፣ ሽልማት አለህ ሲባል መከራውን በደስታ ይቀበላል። ቅዱስ ጴጥሮስም ምንም እንኳ ራሱ ጳውሎስ ቢያውቀውም የሚያውቀውን በርታ አንሞትም በማለት አሳስቦታል። ኅበዝን ተማሪ እንዳትሰንፍ/አትስነፍ) ብሎ መምከር ቀድሞ ሰነፍ መሆኑን

የሚገልጽ ሳይሆን በነበረው ጉብዝና እንዲቀጥል ማሳሰብ ነውና። አንሞትም ያለው የነፍስ ሞትን አንሞትም ማለቱ ነው እንጂ የሥጋ ሞትን አይደለም።

**፳፰. የትንሣኤውን ክብር የሚናገር የእግዚአብሔር አገልጋይ የማሕሌታይ ያሬድ ኦሪት ማዘቢያው ወንጌል ጫማው ነው ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ ጫማ ዋና ሲሆን ማዘቢያ (የጫማ ማሰሪያ) ደግሞ ሁለተኛ ነው። የቅዱስ ያሬድ ወንጌል ጫማው ነው ማለቱ በወንጌል አምኖ ወንጌልን በማስተማር ይኖራል ማለት ነው። ኦሪት ማዘቢያው ነው ማለትም ኦሪትን አውቆ ያስተምራል ማለት ነው።

**፳፱. ድንግል ሆይ በሕግ በሆነ ግንኙነት ከኢያቄምና ከሐና ተወለድሽ እንጂ በፍትወት የተፀነስሽ አይደለሽም ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ በሕግ የሆነ ግንኙነት የሚባለው በትክክል ባልና ሚስት የሆኑ ሰዎች የሚያደርጉት ግንኙነት ነው። በስርቆት ሴት ባሏ ካልሆነ ወንድ ጋር፣ ወንድም ሚስቱ ካልሆነች ሴት ጋር ግንኙነት ካደረገ በዚህ ምክንያት የሚፀነሰው ልጅ በፍትወት የተፀነሰ [ዲቃላ] ይባላል (ዕብ.12፥8)። ድንግል ማርያም ግን በእውነት ባልና ሚስት ከሆኑ ከሐናና ከኢያቄም የተወለደች በመሆኗ በፍትወት የተፀነስሽ አይደለሽም ተብላለች።

**፴. የድንግል ማርያም ምግቧ መና የተባለ ምግብ ነበር። መጠጧም የጽሙና መጠጥ ነበር ሲል እንዴት ነው?**

መልስ፦ ድንግል ማርያም በቤተ መቅደስ ሳለች መልአክ ከሰማይ መናን እያመጣላት ትመገብ ነበር። መጠጧ የጽሙና መጠጥ ነው የሚለው በቅኔ መንገድ የተነገረ ነው። ሰማያዊ መጠጥን ትጠጣ ነበር። ይህም ማለት በሰማያዊ መልአክ እጅ የመጣን ምግብና መጠጥ ትመገብ ነበር ማለት ነው። ያ ምግብ ከየት እንደመጣ የሚያውቀው አምጪው መልአክ ነው። የጽሙና መጠጥ ያለው ጽሙና ወርቅ ነው። ድንግል ማርያም ዝምተኛ ነበረች ለማለት ነው።

**፴፩. አመ ይነግሥ ወልድ በደብረ ጽዮን ክፍልኒ ድንግል የሚለው እንዴት ነው? ደብረ ጽዮን ማን ናት? ይነግሥ ማለቱስ እንዴት ነው?**

መልስ፦ ደብረ ጽዮን የሚላት ኢየሩሳሌምን ነው። ማዕከለ ምድር በመሆኗ በዚያ በነገሠ ጊዜ አለ እንጂ ዳግም መጥቶ በምድር በሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ላይ በፈረደ ጊዜ ተብሎ ይተረጎማል። "ይነግሥ" የሚለው "ይፈትሕ" ሲል ነው። የነገሠ እንደሚፈርድ ወልድም በኃጥኣንና በጻድቃን ለመፍረድ ይመጣልና ነው። ማርያም ሆይ አድዪኝ ማለቱ አማልጅልኝ ማለቱ ነው።

**፴፪. የካህናተ ሰማይ መልካቸው እንደ መረግድ ነው ሲል ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ መረግድ አንድ ጊዜ ተፈጥሮ የሚኖር መዓድን ነው እንጂ እንደ ደማውያን ፍጥረታት በመውለድ በመዋለድ የሚኖር አይደለም። ካህናተ ሰማይን መልካቸው

እንደመረግድ ነው ማለቱ እንበለ ዘርዕ የተገኙ መሆናቸውን ለማመልከት ነው (ራእ.4፥3 ትርጓሜ)፡፡

**፴፫. ቅዱስ ጊዮርጊስ ሆይ ስምህ እንደ ጊደር ወተት እንደ ገነት ወይን ይጣፍጣል ሲል ምን ማለቱ ነው?**

መልስ፦ የጊደር ወተት ይጣፍጣል፣ የገነት ወይንም እንዲሁ፡፡ የቅዱሳንም ስማቸው ይጣፍጣል፡፡ ይኸውም በባሕርዩ ስሙ የሚጣፍጥ (ጥዑመ ስም) የጌታችን የመድኀኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ በእነርሱ ላይ ስለሚያርፍባቸው ነው፡፡ የጴጥሮስ ጥላ ሕሙማንን የፈወሰው ጴጥሮስ የጌታ ከመሆኑ የተነሣ እንደሆነ የቅዱስ ጊዮርጊስ የስሙ መጣፈጥም የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ሰማዕት ከመሆኑ የተነሣ ነው፡፡

**፴፬. ድንግል ማርያም ስለምን በንጹሕ ዝናም ተመሰለች? እንተ በአማን ንጹሕ ዝናም ራሱ ጌታ አይደለም? እርሷ ዝናም ንጹሕ ከተባለች እርሱንስ በምን እንመስለው?**

መልስ፦ ድንግል ማርያምን በንጹሕ ዝናም ስንመስላት ክርስቶስን በልምላሜ፣ በፍሬ እንመስለዋለን፡፡ ከንጹሕ ዝናም ጥሩ ልምላሜ፣ ጥሩ ፍሬ ይገኛል፡፡ ከድንግል ማርያምም ፍሬ ሕይወት ኢየሱስ ክርስቶስ ተገኝቷል [ተወልዷልና] ነው፡፡ በሌላ መልኩ ድንግል ማርያም በደመና ክርስቶስ በንጹሕ ዝናም ይመሰላል፡፡ ነፋስ ባላጠቆራት በነጭ ደመና [ዕራቃ ደመና] ስትመሰል መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለበት በመሆኗ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ የሕይወት ውሃ ክርስቶስ ከእርሷ መገኘቱን [መወለዱን] ያመለክታል፡፡ በትርጓሜ ጊዜ ሕገ ምሳሌ አንዱ ነገር ለብዙ መመሰል ይችላል፡፡ ለብዙ መመሰል ብቻ ሳይሆን እንደ ሁኔታው ለተቃራኒ ነገሮች ምሳሌም የሚሆንበት አጋጣሚ አለ፡፡ ለምሳሌ ጨረቃ ለጻድቃንም ለኃጥኣንም ምሳሌ ትሆናለች፡፡ ጨረቃ አንዴ ብርሃኗ ሲጎድል አንዴ ሲሞላ እንደምትኖር ሁሉ ጻድቃንም ሲወድቁ ሲነሡ ይኖራሉና ነው፡፡ ጨረቃ ከሞላች በኋላ ሕፀፀ ብርሃን እያደረገች እንደምትሔድ ሁሉ ኃጥኣንም ከጽድቅ እየቀነሱ ከኃጢአት እየጨመሩ ይሄዳሉና፡፡

**፴፭. ወአፀዱኒ መላእክት እሙንቱ ሲል ከምጽአት መላእክት ምን አላቸው?**

መልስ፦ በምጽአት ጊዜ ፈራጁ ራሱ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ በምጽአት ጊዜ ምልጃም የለም፡፡ ምልጃ ያለ እስከ ዕለተ ምጽአት ብቻ ነው፡፡ አጫጆቹ መላእክት ናቸው ለሚለው ዓረፍተ ነገር መነሻ ጥቅሱ "ተዉአቸው እስከ መከር ጊዜ አብረው ይደጉ፡፡ በመከር ጊዜም አጫጆችን እንክርዳዱን አስቀድማችሁ ልቀሙ በእሳትም ለማቃጠል በየነዶው እሰሩ፡፡ ስንዴውን ግን በጎተራዬ ክተቱ እላለሁ አለ" የሚለው ቃል ነው (ማቴ.13፥30)፡፡ መላእክት አጫጆች መባላቸው በምጽአት ጊዜ መለከት ስለሚነፉ ንቃሕ መዋቲ ብለው አዋጅ ስለሚናገሩ ነው፡፡ እንጂ ያን ጊዜ ፍርድ የሚሰጠውስ ራሱ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡

፴፮. አብ የፍዳ ልብስን በለበሰ ጊዜ በሚያስፈራ አደባባይ በሚወቅሰን ጊዜ ሲል ምን ማለት ነው አብ ተገልጦ ይታያል እንዴ?

መልስ፦ በምጽአት ጊዜ የሚፈረደው ፍርድ የሦስቱ ማለትም የአብም የወልድም የመንፈስ ቅዱስም ፍርድ ነው። አብ የፍዳ ልብስን በለበሰ ጊዜ የሚለው በፈረደ ጊዜ ማለት ነው። የሦስቱን የአንድነት ግብር ለአንዱ አካል አድሎ መናገር መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው። ስለዚህ ከዚህ የተጠቀሰው አብ ቢሆንም ወልድ የፍዳ ልብስን በለበሰ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ የፍዳ ልብስን በለበሰ ጊዜ ማለት ነው። በሀገራችን ቢቱ የሚባል ከሓዲ በምጽአት የሚፈርድ ወልድ ብቻ ነው እንጂ አብና መንፈስ ቅዱስ አይፈርዱም ብሎ ነበር። በዘመኑ የነበረው ታላቁ ሊቅ አባ ጊዮርጊር ዘጋስጫ ጥሩ ምላሽ ሰጥቶታል። ያን ጊዜ በምጽአት አብ በአካል ባይታይም በፍርዱ ይታወቃል ማለት ነው።

፴፯. ክርስቶስን በቆላ እንዳለ የሱፍ አበባ የቅዱሳን መዓዛቸው ነህ ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ልምላሜ ከሌለበት በረሃ የሱፍ አበባ ሲታይ ደስታን ይሰጣል። የሱፍ አበባ መዓዛም ለሚሸተው ጥሩ መዓዛ አለው። ክርስቶስም የሰው ልጆች ሁሉ በመከራ በነበሩበት ዘመን ከድንግል ማርያም የተወለደ ነውና። ክርስቶስን የሚከተለው ሰውም መዓዛ ነፍስን አግኝቶ ይድናልና ይህንን በምሳሌ ለመግለጽ ነው።

፴፰. ክርስቶስን በእምነት ቃል ያመሰግኑት ዘንድ ዛሬ ሰውና መላእክት አንድ መንጋ ሆኑ ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ አንድ መንጋ ሆኑ ማለት አንድ ማሕበር ሆኑ ማለት ነው። እግዚአብሔርን በማመስገን መላእክትና ሰዎች አንድ ናቸው። በልደቱ ጊዜ እረኞችና መላእክት አንድ ሆነው "ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር" በማለት አመስግነው ነበር። በሌሎች ቅዱሳት በዓላትም በቅድስት ቤተክርስቲያን መላእክት በሥውር ሰዎች በገሐድ ያመሰግናሉና ይህንን ለመግለጽ ነው።

፴፱. አንተን ሁልጊዜ ያዩ ዘንድ አቤቱ የዕውቀት ዓይኖችን ስጠን ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ይህ ቃል ቅዳሴ እግዚእ ላይም ይገኛል። የዕውቀት ዐይን የተባለው ዐይነ ነፍስ ነው። ዐይነ ነፍሳችን ሁልጊዜ አንተን ያይ ዘንድ አድርገን ማለት ነው።

፵. ከንፈሮቿ እንደ ቀይ አበቦች ቀይ ናቸው ሲል እንዴት ነው?

መልስ፦ በዓለም ላይ ከኢየሱስ ክርስቶስ ቀጥሎ ድንግል ማርያምን በመልክ የሚተካከላት አልነበረም። በተፈጥሯዊ መልኳ ከንፈሮቿ እንደ ቀይ አበባ ያማሩ ነበሩ ማለት ነው። በተጨማሪ ከንፈሮቿ ማለት ሃይማኖቷና ምግባሯ ያማረ ነው ማለት ነው (መሓ. መሓ. 4፥3 ትርጓሜ)።